# የገንዘብ ሚኒስቴር

## በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመንግሥት በጀት ለሚሸፈኑ ወጪዎች የክፍያ ተመን መመሪያ ቁጥር 913/2014

የገንዘብ ሚኒስቴር
ሰኔ 2014 ዓ.ም

## መግቢያ

መንግሥት ለትምህርት ሴክተሩ በተለይም ለከፍተኛ ትምህርት ፍትሃዊ ተደራሽነት በሰጠው ልዩ ትኩረት ከጊዜ ወደ ጊዜ በዘርፉ ከፍተኛ ለውጥ እየተመዘገበ መጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሰፋ ያለ መዋዕለ ነዋይ የሚፈስባቸው ግዙፍ የግንባታ ስራዎች የሚከናወንባቸው እና ለመማር ማስተማር፣ ለምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት በርካታ ወጪ የሚፈልጉ በባህሪያቸው ከሌሎች ሴክተሮች የተለዩ በመሆናቸውና ሴክተሩ በመንግሥት የሚመደበውን ሀብትም ይሁን ተቋማት በራሳቸው የሚያመነጩት ሀብት ለተቋማት ተልዕኮ መሳካት እንዲያውሉት አስቻይ የሆነ ግልጽ ሥርዓት እንዲኖራቸው በማስፈለጉ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመንግሥት በጀት ለሚሸፈኑ ወጪዎች የክፍያ ተመን መመሪያ ቁጥር 56/2011 ወጥቶ በሥራ ላይ መዋሉ ይታወቃል፡፡

ሆኖም በመመሪያው አፈፃፀም ባጋጠሙ ችግሮችና በተለይም በ2003 ዓ/ም ከወጣው የመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያ መመሪያ ጋር በተያያዘ ያጋጠመውን የአተገባበር ችግር በማስመልከት በተደጋጋሚ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች እየተነሱ ስለሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ጥያቄዎች በሚመልስ መልኩ ማስተካከል አስፈልጓል፣

እንዲሁም ተመን ያልወጣላቸው ክፍያዎችና ተመኖች በመኖራቸውና የተሻሻለ የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት ያስችል ዘንድ ተመኖችና ተመን ያልወጣላቸው ክፍያዎች ትክክለኛ የአሠራር ሥርዓት ለመፍጠር እና የነበረውን የአሠራር ክፍተት ለመዝጋት ይህንን መመሪያ ማውጣት አስፈልጓል፡፡

በመሆኑም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመማር ማስተማር፣ በጥናትና ምርምር፣ በማህበረሰብ አገልግሎት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር፤ በተቋም አመራርና አስተዳደር፤ እንዲሁም የመማር ማስተማሩን ሂደት በተግባር ትምህርት ለሚያግዙ የቴክኒክ ረዳትነት ስራዎች ከጫና በላይ እና ከመደበኛ ስራ ውጪ ለተከናወኑ ተግባራት የሚከፈሉ ክፍያዎችን ተመን በወጥነት በማዕከል በማዘጋጀት የሚከፈሉ ክፍያዎች ሕጋዊ መሰረት እንዲኖራቸው በማድረግ የህዝብና የመንግስት ሃብት አጠቃቀም ውጤታማነት ለማስጠበቅ ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አውጭው ባለሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 75 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመንግሥት በጀት ለሚሸፈኑ ወጪዎች የክፍያ ተመን መመሪያ ቁጥር 913/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1/ **"ከፍተኛ ትምህርት"** ማለት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ መሠረት የሚተዳደሩ የመንግሥት ዩኒቨርስቲዎችን በሙሉ ያጠቃልላል፤

2/ **"የክፍያ ተመን"** ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመንግሥት በጀት ለሚሸፈኑ ወጪዎች ክፍያ የሚፈፀምበት ተመን ነው፤

3/ **"እጥረት የሚታይበት ሙያዎች"** ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚሰጥ አገልግሎት በገበያ ውስጥ የማይገኙ እጥረት ያለባቸው ሙያዎች ናቸው፡፡

4/ **"ተጋባዥ መምህር"** ማለት በከፍተኛ ደረጃ እጥረት በሚታይባቸው የሙያ መስኮች ልምድ፣ እውቀት እና ተገቢው የትምህርት ዝግጅት ያላቸውን መምህራን ከሌላ ዩኒቨርሲቲ፣ ከኢንዱስትሪ እና ከምርምር ኢንስቲትዩቶች የሚጋበዙትን መምህራን የሚመለከት ነው፡፡

5/ **"የውጭ ፈታኞች ክፍያ"** ማለት የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ እና ከፍ ባለ የአካዳሚያዊ ደረጃ ባሉ ምሁራኖች የልምድ፤ የእውቀት እና የክህሎት ሽግግር በዕጩ ምሩቃን እና በውስጥ አካዳሚያዊ ምሁራኖች ላይ ለማስረፅ ሲባል የሚከፈል ክፍያ ነው፡፡

6/ **"ከጫና በላይ (Over load) ክፍያ"** ማለት በየከፍተኛ ትምህርት ተቋማቸው የሚያስተምሩ መምህራን በሣምንት ማስተማር ከሚጠበቅባቸው 12 ክሬዲት ሃወር በላይ ሲያስተምሩ እያንዳንዱን አካዳሚያዊ ስራ በማስላት እና ተግባራዊነቱ ለተረጋገጠ ስራ የሚከፈል ክፍያ ማለት ነው፡፡

7/ **"የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት ባለሙያ"** ማለት የመማር ማስተማርን፣ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ስራን በሙያው ለማገዝ የተቀጠረ ሠራተኛ ነው፡፡

8/ **"የተግባር ትምህርት"** ማለት በቤተሙከራ (በወርክሾፕ) በኢንዱስትሪ ውስጥ በልህቀት ማዕከላት በማስተማሪያ ሆስፒታል እና ሌሎች በመስክ በተግባር ተደግፎ የሚሰጥ ትምህርት ማለት ነው፡፡

9/ **"ቤተ-ሙከራ"** ማለት ለተፈጥሮ ሳይንስ፣ ማህበራዊ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ ትምህርት እና ሌሎች የተግባር ትምህርት ላላቸው የትምህርት ክፍሎች በአንድ ክፍል በተደራጁ መሣሪያዎች በመጠቀም ሙከራ የሚደረግበት ክፍል ነው፡፡

10/ **"የመስክ የተግባር ትምህርት"** ማለት ለተፈጥሮ ሳይንስ፣ ማህበራዊ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ትምህርትን በተግባር አስደግፎ በመስክ የሚሰጥ ትምህርት ነው፡፡

11/ **"ወርክ ሾፕ"** ማለት የተለያዩ መሣሪያዎችንና ማሽኖችን የያዘ የሳይንስና ቴክኖሎጅ መሣሪያዎችንና ማሽኖችን በመጠቀም ተግባራዊ ትምህርት የሚሰጥበት ክፍል ነው፡፡

12/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴት ፆታን ይጨምራል፡፡

13/ **"ሚኒስትር እና ሚኒስቴር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የገንዘብ ሚኒስትር እና የገንዘብ ሚኒስቴር ማለት ነው፤

4. ***<u>የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን</u>***

ይህ መመሪያ በሁሉም የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## <u>በመንግሥት በጀት ለሚሸፈኑ ክፍያዎች ተመን</u>

5. ***<u>መማር ማስተማርን የሚመለከቱ</u>***

1/ የመምህራን እጥረት ባለባቸው የትምህርት መስኮች የተጋባዥ መምህራን በተባባሪ ፕሮፌሰር እና ከዚያ በላይ ደረጃ የክፍያ የተመን መጠን አከፋፈል በሰዓት ብር 250.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) ይከፈላል፤

2/ የመምህራን ዕጥረት ባለባቸው የትምህርት መስኮች የተጋባዥ መምህራን በረዳት ፕሮፌሰር ደረጃ የክፍያ ተመን መጠን በሰዓት ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) ይከፈላል፤

3/ የመምህራን ዕጥረት ባለባቸው የትምህርት መስኮች የተጋባዥ መምህራን ሌክቸረር ደረጃ የክፍያ ተመን መጠን አከፋፈል በሰዓት ብር 165.00 (አንድ መቶ ስልሳ አምስት ብር) ይከፈላል፤

4/ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቸው የሚያስተምሩ በተባባሪ ፕሮፌሰርነትና እና ከዚያ በላይ ላሉ መምህራን ከሚጠበቅባቸው አካዳሚያዊ ጫና በላይ (Overload) ሲያከናውኑ እያንዳንዱን አካዳሚያዊ ስራ በማስላት እና ተግባራዊነቱ ለተረጋገጠ ስራ በክሬዲት ሀወር 250.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) ይከፈላል፡፡

5/ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቸው የሚያስተምሩ በረዳት ፕሮፌሰርነት ላሉ መምህራን ከሚጠበቅባቸው አካዳሚያዊ ጫና በላይ (Overload) ሲያከናውኑ እያንዳንዱን አካዳሚያዊ ስራ በማስላት እና ተግባራዊነቱ ለተረጋገጠ ስራ በክሬዲት ሀወር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) ይከፈላል፡፡

6/ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቸው የሚያስተምሩ በሌክቸረር ደረጃ ላሉ መምህራን ከሚጠበቅባቸው አካዳሚያዊ ጫና በላይ (Overload) ሲያከናውኑ እያንዳንዱን አካዳሚያዊ ስራ በማስላት እና ተግባራዊነቱ ለተረጋገጠ ስራ በክሬዲት ሀወር 165.00 (አንድ መቶ ስድሳ አምስት ብር) ይከፈላል፡፡

7/ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቸው በረዳት ምሩቅ I እና II ደረጃ ላሉ ረዳት መምህራን ከሚጠበቅባቸው አካዳሚያዊ ጫና በላይ (Overload) ሲያከናውኑ እያንዳንዱን አካዳሚያዊ ስራ በማስላት እና ተግባራዊነቱ ለተረጋገጠ ስራ በክሬዲት ሀወር 100.00 (አንድ መቶ ብር) ይከፈላል፡፡

8/ ከመደበኛው ፕሮግራም ውጭ በዕረፍት ጊዜያቸው በመንግሥት በጀት በክረምት የሚማሩትን ለሚያስተምሩ የሀገር ውስጥ መምህራን ክፍያ በተባባሪ ፕሮፌሰር እና ከዚያ በላይ ደረጃ የክፍያ ተመን መጠን አከፋፈል በሰዓት ብር 250.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) ይከፈላል፤

9/ ከመደበኛው ፕሮግራም ውጭ በዕረፍት ጊዜያቸው በመንግሥት በጀት በክረምት የሚማሩትን ለሚያስተምሩ የሀገር ውስጥ መምህራን ክፍያ በረዳት ፕሮፌሰር ደረጃ የክፍያ ተመን መጠን አከፋፈል በሰዓት ብር 210.00 (ሁለት መቶ አስር ብር) ይከፈላል፤

10/ ከመደበኛው ፕሮግራም ውጭ በዕረፍት ጊዜያቸው በመንግሥት በጀት በክረምት የሚማሩትን ለሚያስተምሩ የሀገር ውስጥ መምህራን ክፍያ ሌክቸረር ደረጃ የክፍያ ተመን መጠን አከፋፈል በሰዓት ብር 175.00 (አንድ መቶ ሰባ አምስት ብር) ይከፈላል፤

11/ ከመደበኛው ፕሮግራም ውጭ በእረፍት ጊዜያቸው በመንግሥት በጀት በክረምት የሚማሩትን ለሚያስተምሩ የሀገር ውስጥ መምህራን ክፍያ ረዳት ምሩቅ I እና II ደረጃ የክፍያ ተመን መጠን አከፋፈል በሰዓት ብር 110.00 (አንድ መቶ አስር ብር) ይከፈላል፤

12/ ከመደበኛው ፕሮግራም ውጭ በዕረፍት ጊዜያቸው በመንግሥት በጀት በክረምት የሚማሩትን የተግባር ትምህርት ለሚያስተምሩ ቺፍ አካዳሚክ ቴክኒካ ረዳት ባለሙያዎች I እና II የክፍያ ተመን መጠን አከፋፈል በሰዓት ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) ይከፈላል

13/ ከመደበኛው ፕሮግራም ውጭ በዕረፍት ጊዜያቸው በመንግሥት በጀት በክረምት የሚማሩትን የተግባር ትምህርት ለሚያስተምሩ ሲኒየር አካዳሚክ ቴክኒካ ረዳት ባለሙያዎች የክፍያ ተመን መጠን አከፋል በሰዓት ብር 150.00( አንድ መቶ ሃምሳ ብር) ይከፈላል፤

14/ ከመደበኛው ፕሮግራም ውጭ በዕረፍት ጊዜያቸው በመንግሥት በጀት በክረምት የሚማሩትን የተግባር ትምህርት ለሚያስተምሩ ቴክኒካ ረዳት ባለሙያዎች የክፍያ ተመን መጠን አከፋፈል በሰዓት ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) ይከፈላል፤

15/ የካሪኩለም የውጪ ገምጋሚዎችን ክፍያ በሚፀድቅ ካሪኩለም ብር 6,000.00 (ስድስት ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡ የትራንስፖርት፣ የአየር ትኬት ወይም የመኪና አገልግሎት፣ ምግብና የመኝታ በተቋማቱ ይሸፈናል፡፡

16/ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች (ሁለተኛ ዲግሪ) ጥናትና ምርምር ወረቀት ለሚፈትኑ የውጪ ፈታኞች ክፍያ በመመረቂያ ፁሑፍ ብር 3,500.00 (ሦስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ይከፈላል፡፡ የትራንስፖርት፣ የአየር ትኬት ወይም የመኪና አገልግሎት፣ ምግብና የመኝታ በተቋማቱ ይሸፈናል፡፡

17/ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች (ሁለተኛ ዲግሪ) ጥናትና ምርምር ወረቀት ለሚፈትኑ የውስጥ ፈታኞች ክፍያ በመመረቂያ ፁሑፍ ብር 2,500.00 (ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) ይከፈላል፡፡

18/ የእንስሳት ህክምና (DVM) የተመራቂ ተማሪዎች የመመረቂያ ፁሑፍ ለሚፈትኑ የውጪ ፈታኞች ክፍያ ብር1,500.00 (አንድ ሺህ አመስት መቶ ብር) ይከፈላል፡፡ የትራንስፖርት የአየር ትኬት ወይም የመኪና አገልግሎት፣ ምግብና የመኝታ በተቋማቱ ይሸፈናል፡፡

19/ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች (3ኛ ድግሪ) ጥናት ወይም የምርምር ወረቀት የውስጥ ፈታኞች ክፍያ በመመረቂያ ጽሑፍ ብር 7000.00 (ሰባት ሺህ ብር) ይከፈላል፣

20/ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች (3ኛ ድግሪ) ጥናት ወይም ምርምር ወረቀት የውጭ ፈታኞች ክፍያ በመመረቂያ ጽሁፍ ብር 10,000.00 (አስር ሽህ ብር) ይከፈላል፣ ትራንስፖርት ወይም የአየር ትኬት ወይም መኪና አገልግሎት፣ ምግብና መኝታ በተቋማት ይሸፈናል፡፡

21/ ደጋፊ የመማሪ ፁሑፍ ላዘጋጁ የሚከፈል በሰነድ ባለ 1 ክሬዲት ከ50-75 ገጽ ብር5,000.00 (አምስት ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡

22/ ደጋፊ የመማሪ ጹሑፍ ላዘጋጁ የሚከፈል በሰነድ ባለ 2 ክሬዲት ከ75-100 ገጽ ብር 7,000.00 (ሰባት ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡

23/ ደጋፊ የመማሪ ፁሑፍ ላዘጋጁ የሚከፈል በሰነድ ባለ 3 ክሬዲት ከ100-150 ገጽ ብር8,500.00 (ስምንት ሺህ አምስት መቶ ብር) የሚከፈል ሆኖ የመማሪያ መጽሐፉ የባለቤትነት መብት የዩኒቨርሲቲው ይሆናል፡፡

24/ ደጋፊ የመማሪያ መጽሐፍ ላዘጋጁ የሚከፈል በሰነድ ባለ 4 እና በላይ ክሬዲት ከ150-200 ገጽ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) የሚከፈል ሆኖ የመማሪያ መጽሐፍት የባለቤትነት መብት የዩኒቨርሲቲው ይሆናል፡፡

25/ የላቦራቶሪ/ወርክ ሾፕ መመሪያ ላዘጋጁ የሚከፈል እስከ 80 ገጽ በሰነድ ብር 5,500.00 (አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ይከፈላቸዋል፡፡

26/ የላቦራቶሪ/ወርክ ሾፕ መመሪያ ላዘጋጁ የሚከፈል ከ80-120 ገጽ በሰነድ ብር 6,500.00 (ስድስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ይከፈላቸዋል፡፡

27/ የላቦራቶሪ/ወርክ ሾፕ መመሪያ ላዘጋጁ የሚከፈል ከ120 ገጽ በላይ በሰነድ ብር 8,000.00 (ስምንት ሺህ ብር) ይከፈላቸዋል፡፡

28/ የሥልጠና ሞጁል ላዘጋጁ የሚከፈል እስከ 80 ገጽ ሰነድ ብር 6,000 (ስድስት ሺህ ብር) የሚከፈላቸው ሆኖ ሞጁል ሪቪው የተደረጉ መሆን እንዳለባቸውና የሞጅሉ ባለቤትነት የዩኒቨርሲቲው ይሆናል፡፡

29/ የሥልጠና ሞጁል ላዘጋጁ የሚከፈል ከ80-120 ገጽ ሰነድ ብር9,000.00 (ዘጠኝ ሺህ ብር) የሚከፈላቸው ሆኖ ሞጁል ሪቪው የተደረጉ መሆን እንዳለባቸውና የሞጅሉ ባለቤትነት የዩኒቨርሲቲው ይሆናል፡፡

30/ የሥልጠና ሞጁል ላዘጋጁ የሚከፈል ማትጊያ ከ120 ገጽ በላይ በሰነድ ብር12,000.00 (አስራ ሁለት ሺህ ብር) የሚከፈላቸው ሆኖ ሞጁል ሪቪው የተደረጉ መሆን እንዳለባቸውና የሞጅሉ ባለቤትነቱ የዩኒቨርሲቲው ይሆናል፡፡

31/ ማየት ለተሳናቸው ተማሪዎች የትምህርትና ማህበራዊ ድጋፍ በወር ብር 250.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) ይከፈላቸዋል፡፡

32/ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ በወር የሚከፈለው ቋሚ ሠራተኛ ይቀጠራል፡፡

33/ ማየት ለተሳናቸው ተማሪዎች የፈተና አንባቢ በአንድ ፈተና ብር 90.00 (ዘጠና ብር) ይከፈለዋል፡

34/ ተቋማት ለተጋባዥ መምህራን ትራንስፖርት፣ምግብና መኝታ ያቀርባሉ፡፡

6. <u>ምርምር ማህበረሰብ አሳታፊነት ኮንፈረስ፣ ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ትምህርታዊ ገለፃዎች የሚመለከቱ፡፡</u>

1/ በተመራማሪዎች ለሚካሄዱ ቴማቲክ የጥናትና ምርምር፣ ማህበረሰብ አገልግሎት፣ ቴክኖሎጂ ሽግግር ንድፈ ሀሳብ ፕሮፖዛል ገምጋሚዎች የሚከፈል ክፍያ በወረቀት/ሰነድ ብር 2,100.00 (ሁለት ሺህ አንድ መቶ ብር) ሆኖ የጥናትና ምርምር ንድፈ ሃሳቦቹ ግራንድ የሆኑና በየደረጃው የማጣራት ስራ ተከናውኖ ለመጨረሻ ግምገማ የሚቀርቡበት ብቻ የሚመለከት ይሆናል

2/ የጥናትና ምርምር ኮንፈረስ ወረቀት የውጪ አቅራቢዎች በወረቀት ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ ብር) ይከፈላቸዋል፡፡

3/ የጥናትና ምርምር ኮንፈረስ ወረቀት የውጪ አቅራቢዎች በወረቀት በግለሰብ ብር 3,000.00 (ሶስት ሺህ ብር) ይከፈላቸዋል፡፡

4/ የምርምር ኮንፈረስ ርዕስ አጀንዳ ወረቀት የውስጥ የመድረክ መሪዎች በአንድ ምዕራፍ ብር 1,500.00 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) ይከፈላቸዋል፡፡

5/ የምርምር ኮንፈረስ ርዕስ አጀንዳ ወረቀት የውጪ የመድረክ መሪዎች በአንድ ምዕራፍ ብር 2,400.00 (ሁለት ሺህ አራት መቶ ብር) ይከፈላቸዋል፡፡

6/ ኮንፈረንስ ላይ ቁልፍ መልዕክት አቅራቢዎች በኮንፈረንስ /በመድረክ/ ብር 6,000.00 (ስድስት ሺህ ብር) ይከፈላቸዋል፡፡ ከሙያው/ርዕሱ ጋር ተያያዥ እና መሪ መልዕክት ለማስተላለፍ በጥናት የታገዘ ዝግጅት ይፈልጋል፡፡

7/ ተቋማት በሚኖራቸው ምርምር ጆርናሎች ላይ በዋና ኤዲተርነት ለሚያገለግሉ የሚከፈል በወር ብር 3,500.00 (ሦስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ይከፈላቸዋል፡፡

8/ ተቋማት በሚኖራቸው ምርምር ጆርናሎች ላይ በተባባሪ ኤዲተርነት ለሚያገለግሉ የሚከፈል በወር ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ ብር) ይከፈላቸዋል፡፡

9/ ለምርምር ስነ ምግባር (Ethical Clearance) Review Board አካላት የሚደረግ ክፍያ በግለሰብ በወር ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ ብር) ይከፈለዋል፡፡

7. <u>ተቋም አመራርና አስተዳደርን የሚመለከቱ</u>

1/ ወርክሾፖችና ሲምፖዚየሞችን ለሚያዘጋጁ፣ ለሚያስተባብሩና ለራፖርተሮች የሚከፈል በኮንፈረንሶች፣ በወርክሾፖችና ሲምፖዚየሞች ብዛት በኩነት ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ ብር) ተከፋይ ይሆናሉ

2/ በማእከል /በዩኒቨርሲቲ በእቅድ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አካላት የአቅም ግንባታ ሥልጠና ለሰጡ የሚደረግ ክፍያ በሥልጠና ርዕስ /በግለሰብ 3,000.00 (ሦስት ሺህ ብር) እንዲከፈል ይደረጋል፡፡

3/ በክረምት ወራት በመንግስት በጀት መድቦ እንዲማሩ ለሚደረጉ ተማሪዎች አገልግሎት በዕረፍት ጊዜያቸው በአመቱ ተጨማሪ አስተዳደራዊ ስራ ለሚሰሩ አስተዳደር ሠራተኞች በግለሰብ የአንድ ወር ደመወዝ እንዲከፈል የሚደረግ ሲሆን የሚሰሩት ስራ ክፍል ጸባይ ምክንያት የዓመት ዕረፍት መውሰድ የማይችሉትን ብቻ የሚመለከት ይሆናል፡፡

4/ የተማሪዎች ህብረት አመራር እና የክበባት አመራር የሞባይል ካርድ ክፍያ በወር ብር 350.00 (ሦስት መቶ ሃምሳ ብር) በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ብቻ ላሉ የስራ አስፈፃሚ አባል ለሆኑት የሚከፈል ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

### 8. መመሪያውን ስለ ማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሚኒስትሩ ሊሻሻል ይችላል፡፡

### 9. የተሻሩ መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮችና የአሰራር ሥርዓቶች

1. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመንግሥት በጀት ለሚሸፈኑ ወጪዎች የክፍያ ተመን መመሪያ ቁጥር 56/2011 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡
2. ይህን መመሪያ የሚቃረኑ መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮችና የአሰራር ሥርዓቶች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

### 10. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሰኔ 24 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ሰኔ 24 ቀን 2014 ዓ.ም.*

*አህመድ ሺዴ*
*የኢፌዲሪ ገንዘብ ሚኒስቴር*
*ሚኒስትር*